# ሰሞነ ሕማማት



ሰሞነ ሕማማት የመጨረሻው የጾም ሳምንት ሲሆን በሆሣዕና እሁድ ድንጋዮች የዘለሉለት፤ ጡት የሚጠቡ ሕጻናት አንደበታቸው ተከፍቶ ያመሰገኑት አምላክ በዚህ ሳምንት ተሸጦ፣ አሳልፎ ተሰጥቶ፣ ተገርፎ፣ ተሰቃይቶ፣ ለእኛ ሲል በቀራንዮ የመስቀል ሞት የቀመሰበት ከዚያም ሞትን ድል አድርጎ እኛን የዋጀበት ሳምንት ነው።

# የሆሣዕና እሁድ



በዚህ ዕለት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ «በጌታ ስም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ ነው። በሰማይ ሰላም በአርያምም ክብር» እያሉ አመሰገኑት።

ሆኖም ግን ይህ ሁሉ ውዳሴ ብዙም አልቆየ። ከጥቂት ቀናት በኋላ መልሰው ስቀለው ስቀለው እያሉ ብዙዎች ጮኹ።



እኔስ ታዲያ ዛሬ የማመሰግነውን ጌታዬን «ከፍ ከፍ በል፤ ክበር ተመስገን ...» የምለውን አምላኬን ነገ አሳልፌ እሰጠው ይሆን?

ሰማይ ዙፋኑ ምድርም የእግሮቹ መረገጫ የሆነ አምላክ እሱ የኛን እግር ዝቅ ብሎ በማጠብ ትህትናን ሊያስተምረኝ ሲወድ የእኔ ልብ ም ነው ለመታዘዝ የደነደነ ሆነ?



መድኃኒቴና አምላኬ ጌታዬም ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኔ የተቀበለውን መከራ እና የፍቅሩን ጥልቀት እንዴት አድርጌ ለመረዳት እችል ይሆን?

የማወቅና ማስተዋሉ ጥበብ ቢኖረኝማ ዕለት ዕለት እንድሸከመው የሚገባኝን መስቀል ይዤ እሱን በተከተልኩት ነበር። ስለ ስሙ የሚደርስብኝን መከራ ሁሉ በጸጋና በምስጋና በተቀበልኩት ነበር።



እጆቹ በምስማር ተቸንክረው አምላኬ ለእኔ ያለውን ፍቅር ሲገልጽ አንድም ቃል ከአንደበቱ አልወጣውም። የእኔን በደል እርሱ ሊሸከም እጆቹን እንዲሁ ዘረጋ። ተቸነከረ።

ዛሬ ታዲያ የእኔ እጆች፥

- ወንድሜንና እህቴን ለመርዳት እንደምን አቃታቸው?
- በወንድሞቼና በእህቶቼ መንገድ ላይ የማሰናከያ ድንጋይ ለማስቀመጥ ለምን ይፈጥናሉ?
- አስራትን ለማውጣት፤ በረከትን ከአምላክ ለመቀበል ምነው ተሳናቸው?



በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት እግሮቹ፣
በችንካር ላይ ዋሉ ምንም ሳይሰለቹ።

ታዲያ፥ አምላኬ ለእኔ ያሳየው እና
አሁንም የሚያሳየው የፍቅሩ ጥልቀት
ቢገባኝ ኖሮ እግሮቼ ወደ መቅደሱ
ለመገስገስ ባልሰነፉም ነበር። በቅዳሴው
እና በማሕሌቱ ሰዓት ባልተንቀጠቀጡም
ባልዛሉም ነበር።

የእኔ ሕይወት በሆሣዕና ዕለት አመስግነውት ከቀናት በኋላ እንደከዱት የኢየሩሳሌም ሰዎች ከመሆን በምን ተሻለ?

የሰማይና የምድር ጌታ ተሰድቦ፣ ተገርፎ፣ ተተፍቶበት ሳለ እኔ ለምን ተነካሁ እያልኩ ማጉረምረም የዕለት ዕለት ቋንቋዬ ከሆነ መስቀሉን ይዤ እሱን መከተል ተስኖኛል፤ የመስቀሉም ፍቅር ተሰውሮብኛል ማለት ነው።



«መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም።»

ማቴዎስ 10፥38